# የእንቁላል ብልሽቱ ከውስጥ፤የአሳ.....ከጭንቅላቱ

ስንሻው ሃብታሙ--ከሰሜን አዲስ አበባ

ዓለማችን በተለያዩ ፖለቲካዊ፤ኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ ችግሮች የተተበተበች በመሆኑ በብዙ ሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ሕዝቦቿን ሕልውና በእጅጉ የሚፈታተኑ ክስተቶችን ለማስተናገድ ተገዳለች፡፡ የችግሮቹ ዓይነት፤ ባህሪ፤ምንጭና ደረጃ ይለያይ እንጂ የትኛውም የዓለማችን ክፍልና ህብረተሰብ በአንድ ወይም በሌላ መልኩ ከችግር ፈጽሞ የጸዳ ነው ማለት አይቻልም፡፡ ሃገራት የሚገኙበት ተጨባጭ ፖለቲካዊ፤ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ የእድገት ደረጃ፤ የህብረተሰብ ጥንቅርና ማስተጋብር፤ሥነ-ልቦና፤ባህልና እምነት፤ ተጨባጭ አካባቢያዊና ዓለም አቀፋዊ ሁኔታዎችና ክስተቶች፤ወዘተ የችግሮችን ዓይነትና ባህሪ በዋናነት የሚወስኑ ገጽታዎች ናቸው፡፡

ችግሮች ውስጣዊ ወይም ውጫዊ /አካባቢያዊና ዓለም አቀፋዊ/፤ ቀላልና ከባድ፤የተጠበቁ ወይም ያልተጠበቁ ወዘተ ሊሆኑ እንደመቻላቸውም መፍትሄአቸው በዚያው ማጠን የተለያዩ ሊሆን ይችላል፡፡ አንዳንዶቹን ችግሮች ሃገራት በራሳቸው መንገድና አቅም ተጉዘው መፍትሄ ሊያፈላልጉላቸው ቢችሉም፤አንዳንዶች ግን እንደ ችግሩ ዓይነት፤ባህሪና ስፋት የሌሎችን እገዛ፤የጋራ ጥረትና ዓለም አቀፋዊ ትብብርና ድጋፍ የሚጠይቁ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

ዓለም አቀፋዊ ገጽታ ካላቸው ችግሮች መካከል ሽብርተኝነት አንዱ ዋነኛና ወቅታዊ አጀንዳ ከሆነ ወሎ አድሯል፡፡ በተለያዩ ሃገራትና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ዘንድ ሽብርተኝነት በተወሰነ ደረጃ የተለያዩ ትርጉም ወይም አረዳድ ቢኖረውም በማስረታዊ ትርጉሙ ግን አንዳችም አሻሚነት የለውም፡፡ ሃገራትና አንዳንድ ተቋማት አንድን ድርጅት በሽብርተኝነት ለመፈረጅ በአማዡ ዓለም አቀፋዊ ተቀባይነት ያለውን መመዛኛ ማስረት ባደረገ መልኩ ሆኖም እንደራሳቸው ተጨባጭ ሁኔታ ግንዛቤ ወስጥ የሚገቡ ነጥቦችን ታሳቢ በማድረግ የሚንቀሳቀሱበት ሁኔታ አለ፡፡ ለምሳሌ እኤአ በ2008 ላይ ወጥቶ በነበረ አንድ ሚጃ ማስረት በተለያዩ የዓለም ሃገራት ዘንድ በተለያዩ መልኩና ጊዚያት በሽብርተኝነት የተፈረጁ 130 ያህል ድርጅቶች እንደነበሩ ይፋ አድርጓል፡፡ ከነዚህ ድርጅቶች መካከልም አንዳንዶቹ ሃገራት በተናጠልና ከሁለት በላይ በሆኑ ሃገራትና አብዛኞቹ በአማዡ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ባገኘው ጥቅል መመዛኛ ማስረት፤ በበርካታ ሃገራት የተደገፈና በዓለም አቀፍ ደረጃ በሽብርተኝነት የተፈረጁ ቡድኖች የተካተቱበት ነበር፡፡

ማስረታዊ የሆነውና ሁሉንም ወገኖች በጋራ የሚያግባባው የሽብርተኝነት ትርጉም እንደተጠበቀ ሆኖ፤ በአሁኑ ጊዜ እስከ 100 የሚደርሱ የሽብርተኝነት ትርጉሞች እንዳሉ አንዳንድ ሚጃዎች

ያሳክታሉ። ያም ሆኖ ግን እዚህ ላይ ሊሰመርበት የሚገባው አቢይ ነጥብ ማዕረታዊ ትርጉሙ ሁሉንም በጋራ የሚያግባባ ሆኖ፤ ሌላው ልዩነት አከራካሪ ያልሆነና የሽብርተኝነት ትርጉምን የሚያደበዝዝ ወይም አሻሚ እንዳልሆነ በሁሉም ዘንድ ግንዛቤ የተያዘበት ጉዳይ መሆኑ ነው።

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ሽብርተኝነት በየሃገራቱ የተለያዩ የትርጉም ይዘት አለው የሚል ወሃ የሚይቋጥር ማከራከሪያ አልፎ አልፎ ይነሳ እንጂ፤ ከዚህ በተቃራኒ ግን ሁሉንም በጋራ የሚያግባባወና ጠቅለል ያለው የሽብርተኝነት ትርጉም ተብሎ የሚወሰደው ቀጥሎ የተመለከተው ፍሬ ሃሳብ ነው። ይህ ትርጓሜም የተወሰደው በቀጥታ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ካገኘው የሽብርተኝነት አጠቃላይ ትርጉም በማሳት እንደሆነ አንባቢዎቹ ልብ በሉልኝ።

በመሆኑም በግርድፉ ሲታይ ሽብርተኝነት ማለት፤ አንድን የራስ ዓላማ ለማራመድ በማሰብ በግለሰብ ደረጃ ወይም በቡድን ተደራጅቶ በተቀነባበረ ሴራና ዝግጅት የሕዝብን ወይም የግለሰብን ሰላምና ደህንነት እንዲሁም መንግሥታዊ ሥርዓቱንና ተቋማትን ኢላማ ያደረገና በተለይም ማንንም ሳይለይና ምንም አይነት መከላከያ በሌላቸው ላይ ድንገተኛ ጥቃት ሚድረስና በዚህም ሽብርና ፍርሃት ማስፈን የሚል ነው። በአማዣኙ ይህን በሚድረግም እወቅናን ለማግኘት መሻትና የተወሰነ የሕብረተሰብ ክፍልን በማስገደድ፤ በማስፈራራትና በማሸበር ማለትም በኃይልና በተጽእኖአቸው ሥር በማዋል የዓላማቸው ደጋፊ እንዲሆኑ ሚድረግ ከዚህም አልፎ ዓላቸውን እንዲፈጽሙላቸው ማስገደድ ማለት እንደሆነ በተለያዩ ሃገራትና ተቋማት የጸረ ሽብርተኝነት ሕጎች ወስጥ በግልጽ ሰፍሯል።

ይህን ዓይነት ጸረ ሰላም ድርጊት የሚፈጽሙትም ሕግን በመጣስ፤ የህብረተሰቡን ግለሰብአዊና ማህበራዊ ደህንነት አደጋ ላይ በመጣልና ስጋት በመፍጠር፤ እንዲሁም የዜጎችን ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብት በመደፍጠጥና ብሎም መንግሥታዊ ተቋማት ሕጉ በሚፈቅደው መሰረት ኃላፊነታቸውን በአግባቡ እንዳይወጡ በሚደናቀፍ ነው። የዚህ ድምር ውጤትም በንጹሃን ግለሰቦች ላይ የሕይዎት፤ የአካልና የንብረት ጥፋት፤ በመንግሥትና የሕዝብ መገልገያ በሆኑ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተቋማት ወይም የመሰረተ ልማት አውታሮች፤ በሃገር ሃብትና ንብረት ላይ ወድመት በሚድረስ በአጠቃላይ በዜጎች የእለት ተእለት ሰላማዊ እንቅስቃሴ ላይ አደጋና ስጋት ማጋረጡ ነው።

አሁን ባለው ዓለም አቀፋዊ ተጨባጭ ሁኔታ የትኛውም የዓለም ክፍል ከሽብርተኝነት ጥቃት አለያም ቢያንስ ቢያንስ ከስጋት የጸዳ ነው ማለት አይቻልም። ምክንያቱም የትኛው ቡድን መቼ፤ የትና በማን ላይ ምን ዓይነት ጥቃት እንደሚያደርስ የሚታወቅ ነገር የለም። የሽብር ጥቃት ዓይነቱና ማጠኑ እጅግ እየተራቀቀና አድማሱን እያሰፋ የመጣ ክስተት እየሆነ ማምጣቱን ተከትሎ ሃገራትና

በርካታ ዓለም አቀፋዊ ድርጅቶች በዚህ ረገድ ጠበቅ ያለ የፀረ-ሽብርተኝነት ሕግ በማውጣት ተባብረው በማስራት ላይ ይገኛሉ፡፡

የሽብርተኝነትን ስጋት ግዝፈትና ዓለም አቀፋዊነት ለማንዘብም ችግሩ ይበልጥ ዓለም አቀፋዊ ትኩረት እየሳበ ማምጣት ከጀመረበት እኤአ ከ1970ዎቹ የመጀመሪያ ዓመታት ጀምሮ የደረሱ ጥቃቶችን መጫከቱ ጠቃሚ ይሆናል፡፡ በዚህም ማስረት እኤአ ከ1970-2008 ድረስ በነበሩት ዓመታት ብቻ በተሰባሰበ ሚጃ እንኳ በተለያዩ ሃገራት ከ87 ሺህ በላይ የተለያዬ ይዘት፤ የጉዳት ማጠንና ደረጃ የነበራቸው የተሳኩና ያልተሳኩ የሽብር ጥቃቶች መመዝገባቸወን በዚህ ዙሪያ የተደረጉ ጥናቶች ያማለክታሉ፡፡ በዋናነትም እነዚህ የሽብር ድርጊቶች ሕዝብ በብዛት በሚሰባሰቡባቸው ቦታዎች ለምሳሌ በቤተ እምነት፤በገበያ ስፍራዎች፤በሕዝብ ማዝናኛዎች፤ በጎዳናዎችና አደባባዮች፤በትምህርትና ሌሎች መንግሥታዊና ሕዝባዊ ተቋማት… ወዘተ ላይ የደረሱ ጅምላ ጨራሽ የቦንብ ጥቃቶችን ጨምሮ፤ የተለያዩ የግለሰብና የቡድን እገታዎች፤የአይሮፕላን፤የተሽከርካሪና የሚርከብ ጠለፋዎችና እገታዎች፤በግለሰቦች ወይም በቡድን አባላት ላይ ያነጣጠሩ ግድያዎች፤በመንግሥት ባለሥልጣናትና በፖለቲካ ፓርቲዎች፤በሲቪክና የሙያ ማህበራት አሜራር ዓባላትና ታዋቂ ግለሰቦች፤በጋዜጠኞች፤በረድኤት ድርጅቶች ኃላፊዎችና ሰራተኞች ግድያና እገታ፤እንዲሁም በማስረተ ልማትና በሕዝብ ማጓጓዣ ተሽከርካሪዎችና አውታሮች… ወዘተ ላይ ያነጣጠሩ ማጠነ ሰፊ ጥቃቶች ነበሩ፡፡ በዚህ ዓለም አቀፍ የሽብርተኞች ሪከርድ ዝርዝር ላይ ኢትዮጵያ ወስጥ ተፈጽመው የነበሩ የሽብር ጥቃቶችም ተካተዋል፡፡

ዓለማችንን ሰላምና ብልጽግና የሰፈነባት፤ ለሕዝቦቿ የተስተካከለ ማህበራዊ አኗኗር የተመቸች ለማድረግ የሚደረጉ ጥረቶች መኖራቸው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ከዚህ በተጻራሪው በመቆም ሆን ብሎ የህብረተሰቡን ሰላማዊ ኑሮ የሚያወኩ ተግባራት በአንዳንድ ኃይሎች ሚፈጸማቸው ደግሞ የእለት ተእለት ክስተት ሆኖ መቀጠሉ አልቀረም፡፡ይህ ደግሞ በሌላ ሁኔታ የተከሰቱ ችግሮችን ይበልጥ በማባባስ የራሱ የሆነ ተጽእኖ ይፈጥራል፡፡

በዚህ ረገድም በዓለማችን በስፋት ተንሰራፍተው ከሚስተዋሉ ችግሮች መካከል የሽብርተኝነት አደጋና ስጋት አንዱ እንደመሆኑም ዓለማችን በርካታ ዘግናኝና ጅምላ ጨራሽ የሽብር ጥቃቶችን አስተናግዳለች፡፡ የጉዳቱ ዓይነት፤ ማጠንና ይዘት ወይም ደረጃ ይለያይ እንጂ፤ በነዚህ ጥቃቶች የበርካታ ንጹሃን ዜጎች ህይዎት አለአግባብ ተቀጥፏል፤ የአካል ጉዳት ደርሷል፤በህዝባዊና መንግሥታዊ ተቋማት እንዲሁም በግለሰቦች ሃብትና ንብረት ላይ ማጠነ ሰፊ ጉዳትና ወድመት ተፈጽሟል፡፡ በዚህም በተለያዩ የዓለማችን ክፍሎች በሚኖሩ ሕዝቦችና ንጹሃን ዜጎች ላይ ከፍተኛ ስጋትና ፍርሃት፤በራስ ያለመተማመንና የማጠራጠር መንፈስ እንዲነግሥ ምክንያት ሆኗል፡፡ አልፎ

አልፎም በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ ለእለታዊ ተግባር በየእለቱ በሰላም ወጥቶ በሰላም መግባስና ከቦታ ቦታ በነጻነት መንቀሳቀስ እንደ እድለኝነትና እንደብርቅ የሚቆጠርበት ሁኔታን መመልከት ይቻላል፡፡

በዚህ የሰላም፤የሕዝቦች ደህንነትና ማህበራዊ ሕይዎት ላይ የተጋረጠውን አደጋ ለመቋቋም ሃገራት የየራሳቸውን የተናጠልና ከዚህም ባለፈ ከሌሎች ሃገራትና ተቋማት ጋር/በዓለም አቀፍ ደረጃ/ በጋራና በትብብር በማስራት ጠቃሚ ነው የሚሉትን እርምጃ በመወሰድ ላይ ይገኛሉ፡፡ የሽብር ጥቃት በማንም፤ የትም፤ መቼም ይፈጸም በአንድ ወይም በሌላ መልኩ ድንበር ተሻጋሪ ጉዳት ወይም ወጤት ሊያስከትል የሚችልበት አጋጣሚ ይኖራል፡፡ ለዚህም ነው የሽብር ጥቃትን ለመከላከል፤ሊያስከትል የሚችለውን ጉዳት ለመቀነስ ብሎም ጉዳት ከደረሰ በኋላም ቢሆን ጥፋተኞችን ተከታትሎ ለመያዝና ለፍርድ ለማቅረብ በሚደረጉ ጥረቶች ላይ ሃገራት በትብብር ማስራት እንዳለባቸው የሚመከረው፡፡ በማንኛወም መልኩ የሚፈጸም የሽብር ጥቃት ዓለም አቀፋዊ ገጽታ ያለው በመሆኑም በትብብር ማስራቱ እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡

ወደ ሃገራችን ሁኔታ ስንመለስም ባለፉት ዓመታት የተለያዩ የሃገር ወስጥና የውጭ የሽብርተኛ ቡድኖች ያቀነባበሯቸውና የሞከሯቸው ጥቃቶች መፈጸማቸውን በቁጭትና በከፍተኛ ሃዘን የምናስታወሰው ክስተት ነው፡፡ በነዚህ ጥቃቶች ሳቢያም በርካታ ንጹሃን ዜጎች ሕይዎታቸውን አጥተዋል፤በመንግሥታዊና ሕዝባዊ ተቋማትና አገልግሎት መስጫዎች እንዲሁም በግለሰቦች ሃብትና ንብረት ላይም ጉዳት ደርሷል፡፡ አንዳንድ የተቀነባበሩ የሽብር ጥቃቶችም ሳይሳካላቸው አስቀድሞ በመንግሥትና በህብረተሰቡ የጋራ ጥረት ሊከሽፉ ችለዋል፡፡ አንዳንድ የደረሱ ጥቃቶችንም ተከትሎ የጥፋት መልእክተኞችንና ድርጊት ፈጻሚዎችን በማከታተል ተገቢው ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድባቸው ተደርጓል፡፡

ሽብርተኝነትን በመከላከል ረገድ ሃገራችን በሃገር ወስጥም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያደረገችውና እያደረገችው ያለው ተሳትፎና እንቅስቃሴ አድናቆት አስገኝቶላታል፡፡ በተለይም የሽብር ጥቃቶችን አስቀድሞ ለመከላከል የዘረጋችው የክትትል ስልትና እያደረገችው ያለው ዓለም አቀፋዊ ንቁ ተሳትፎና ትብብር በብዙ መልኩ ችግሩን ለመከላከል እየበረከተ ያለው አስተዋጽኦ ግምት የሚሰጠው ነው፡፡ የሽብርተኛ ቡድኖች እንደ አመሰራረታቸውና የያዙት ዓላማ አካባቢያዊ ወይም ዓለም አቀፋዊ ገጽታ ያላቸው ናቸው፡፡ ያም ሆኖ ግን በመሰረታዊነት ሚያዝ ያለበት ሽብርተኝነት በማንምና በየትም ስፍራ በፈጸም ዞሮ ዞሮ ድርጊቱና የሚያስከትለው ወጤት አሉታዊና ዜጎችን ለከፍተኛ ጭንቀትና ፍርሃት የሚዳርግ በመሆኑ በየትኛወም የዓለም ክፍል በሚኖሩ ሰላማዊ ዜጎች፤ሃገራትና መንግሥታት ምንጊዜም የሚወግዙትና የሚታገሉት ተግባር መሆኑ ነው፡፡

ኢትዮጵያ ቀደም ባሉት ጊዚያት በተደጋጋሚ ከወስጥና ከወጪ የሽብር ኃይሎች በተቃጠባት ጥቃቶች ሰለባ ሆናለች፡ መንግሥትና ዜጎቿም ያልተፈለገ ዋጋ ከፍለዋል፡፡ መንግሥት በዚህ መነሻነትም የራሱን የተናጠል የመከላከል እርምጃ በመውሰድና ከዚያም ባለፈ ከዓለም አቀፍ የጸረ ሽብር ኃይሎች፤ ሃገራትና መንግሥታት ጋር በመተባበር ጠንካራ አጋርነቱን በተግባር እያረጋገጠ ይገኛል፡፡ በምስራቅ አፍሪካም የሽብርተኝነት እንቅስቃሴን በመከላከል ጥረቶች ላይ ያለው የጎላ ተሳትፎ በተደጋጋሚ በአርያነት የሚጠቀስ ነው፡፡ ይህ እርምጃም ሰላምን በማስፈን ረገድ ከሃገራዊ ጠቀሜታው ባለፈ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ፋይዳ ያለው በመሆኑ የራሱ የሆነ አስተዋጽኦ ያለው ነው፡፡

ሽብርተኝነትን መከላከል ለሃገራችን የራሱ የሆነ ልዩ ትርጉም ያለው ነው፡፡ ሃገራዊ ደህንነትን በሁለንተናዊ መልኩ በሚረጋገጥ ልማቱን ከማፋጠንና ከዚህም ጋር የዜጎችን የተረጋጋና ሰላማዊ አኗኗር ከሚረጋገጥ አኳያ ቅደሚያ ትኩረት ከሚሰጣቸው ተግባራት መካከል እንደ አንዱ ተደርጎ የሚወሰድ ነው፡፡ ይህም በአንድ ወይም በሌላ መልኩ እንደ ሕዝብና እንደ ሃገር የመቀጠል ወይም ያለመቀጠል፤ እንዲሁም የሕግ የበላይነትን የማስከበር ወይም ያለማስከበር ውጤት የሚያስከትል በመሆኑ መንግሥት ሽብርተኝነትን በመዋጋት ረገድ እየወሰደ ያለው ገንቢ እርምጃ ከአስፈላጊነቱም በላይ የሕዝብና የሃገር ሕልወናን የማስከበርና የሚረጋገጥ ወሳኝ ጉዳይ ተደርጎ የሚወሰድ ነው፡፡

በዚህ ረገድም ኢትዮጵያ ከዓመት በፊት የፀረ ሽብርተኝነት ሕግ በማውጣት ተግባራዊ ማድረግ ጀምራለች፡፡ የሽብርተኝነት ስጋት ከአንድ ሃገር ክልልም ባለፈ ዓለም አቀፋዊ ችግር እንደመሆኑ፤ ሃገራት እንደራሳቸው ተጨባጭና ነባራዊ ሁኔታ ከዓለም አቀፉ የሽብርተኝነት መመዘኛና ግንዛቤ ጋር በተጣጣመ መልኩ ሕግ አወጥተው መንቀሳቀሳቸው ተቀባይነት ያለው አሰራር ነው፡፡ ይህን መሰረት በማድረግም ነው ኢትዮጵያ የራሷን ሕግ የቀረጸችው፡፡ እዚህ ላይ መነሳት ያለበት መሰረታዊ ጉዳይም በእርግጥስ ኢትዮጵያን በማንኛውም መልኩ ሊቃጣ የሚችል የሽብርተኝነት ጥቃት ያሰጋታል ወይስ አያሰጋትም? የሚለው ጥያቄ ነው መነሳት ያለበት የሚመስለኝ፡፡ በተግባር እንደታየው ከስጋትም ባለፈ በተለያዩ ጊዚያት የሽብር ጥቃቶች የተቃጠባትና የተሞከሩባት እንደመሆኑ የዚህ ጥያቄ ምላሽ ደግሞ ግልጽና አጭር የሆነ አወንታ ነው፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ቀደም ሲል የተፈጸሙ፣ በተወሰኑ ጊዚያትም በተለያዩ ደረጃ የከሸፉ ጥቃቶችን ማስታወስ ተገቢ ነው፡፡ የእነዚያ ጥቃቶች ፈጻሚዎች እነማን እንደነበሩ ደግሞ በግልጽ የታወቁ ስለሆኑ ለዚህም ምላሽ ለማግኘት የተለዩ ምርምርና ጥናት ማድረግን የሚጠይቅ አይደለም፡፡

በተለይም የምስራቅ አፍሪካ ቀንድ የሽብርተኝነት ስጋትና ያለሚጋጋት በከፍተኛ ደረጃ ከተጋረጠባቸው የዓለማችን አካባቢዎች ማካከል አንዱ ዋነኛ ተጠቃሽ እንደማሆኑም፣ ጠንካራ የጸረ-ሽብርተኝነት እርምጃ በተናጠልና በጋራ መውሰድ የግድ ይላል፡፡ ይህን ማሰረት ባደረገ ሜከም ኢትዮጵያ የሕዝቦቿን ሰላምና ብሄራዊ ደህንነቷን ከማስጠበቅ አኳያ፤ ሃገራዊ፤ አካባቢያዊና ዓለም አቀፋዊ ተጨባጭ ሁኔታዎችን ባገናዘበ ሜኩ የተጠና የራሷን የጸረ-ሽብርተኝነት ሕግ አወጥታለች፡፡ የጸረ ሽብርተኝነት አዋጁ መውጣቱን ተከትሎም በቅርቡ በዋናነት ይህንኑ አዋጅ፤ ሃገራዊ፤ አካባቢያዊና ዓለም አቀፋዊ ሁኔታዎችን ማሰረት በማድረግ፤ በኢትዮጵያ በሽብርተኝነት የተፈረጁ ኃይሎችን ለይቶ ያማላከተ ወሳኔ በሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ጸድቋል፡፡ በዚህም ማሰረት ሦስት የሃገር ወስጥና ሁለት የውጭ የሽብር ኃይሎች በሃገሪቱ የሽብርተኝነት ጥቁር ማዝገብ ወስጥ እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡ እነዚህም ከሃገር ወስጥ ኦብነግ፤ ኦነግና ግንቦት ሰባት፤ ከውጭ አልሸባብና አልቃይዳ ናቸው፡፡

እዚህ ላይ የውጮዎችን ለጊዜው ትተን ከሃገር ወስጥ በሽብርተኝነት የተጀፈረጁ ኃይሎች በምን ማስፈርት ይህን ካምፕ ተቀላቀሉ የሚለወን መሜከቱ ተገቢ ይሆናል፡፡ በዚህም ማሰረት ኦነግና ኦብነግ በሃገሪቱ የተፈጠረወን ሰላማዊ፤ ነጻና ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ሜድረክ በሜገጥ እናራምደዋለን የሚሉትን ዓላማ በሃይልና በአሜጽ ለማስካት ብሎም ሕገመንግሥታዊ ሥርዓቱን በኃይል በማናድ የራሳቸወን ተጽእኖና ፍላጎት በሕዝብ ላይ ለመጫን ነፍጥ አንግበው ጫከ የገቡ ናቸው፡ ጫከ መግባትም ብቻ ሳይሆን፤ አንድ የሽብርተኛ ቡድን ሊፈጽመው የሚችለወን አይነት ተግባር ሁሉ በተለያዩ አጋጣሚዎች የፈጸሙና ለሚፈጸምም በዝግጅት ላይ እንዳሉ በተለያዩ ጊዜያት በክትትል ተደርሶባቸው የተጋለጡ ኃይሎች ናቸው፡ ይህ ደግሞ ከበቂ በላይ በሆነ ተጨባጭ ማስረጃ የተረጋገጠ ሃቅ ነው፡

ግንቦት ሰባት የተባለው ድርጅትም ከ1997 ምርጫ ጋር ተያይዞ ተከስቶ የነበረወን ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱን በኃይልና በአሜጽ ለማፍረስ የተቀነባበረው ሴራ ዋነኛ ተዋናዮች በነበሩና በተለይም በዶ/ር ብርሃኑ ነጋ አስተባባሪነት አንዳንድ የቅንጅት አሜራር አባላት በአሜሪካ ያቋቋሙት ድርጅት ነው፡ አማስራረቱም ከውጭ እንደማሆኑ ጸረ ሰላም የሆኑ የአሜራር አባላቶቹም ማሽገው የሚገኙት በዚያው በአሜሪካና በአንዳንድ የአወሮፓ ከተሞች ነው፡ ይህ ድርጅትም ገና ከጥንስሱና ከወልደቱ ጀምሮ ራሱ ይፋ እንዳደረገው በኢትዮጵያ ምንም ዓይነት ህጋዊና ሰላማዊ የሚባል ተሳትፎና ትግል በምንም ሜኩ እንደማይከተልና ከዚህ ይልቅ ከሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ ተሳትፎ ወጭ ኃይልና አሜጽን ጨምሮ የትጥቅ ትግል እንደሚያደርግና በተለይም ማንኛወንም አይነት እርምጃ በመወሰድና በማንቀሳቀስ ሕገ መንግሥታዊወን ሥርዓት እንደሚያፈርስና መንግሥትን ለመጣል እንደማንቀሳቀስ አስታወቋል፡፡ ይህ እንግዲህ የግንቦት ሰባት "ግልጽ ሚፌስቶ" ሊባል የሚችል

ነው፡፡ ማንኛውንም ዓይነት እንቅስቃሴና እርምጃ ማለት ደግሞ የሽብር ጥቃትና የኃይል እርምጃም እንደ አንዱ አማራጭ ተደርጎ የሚወሰድ እንደሆነ ድርጅቱ በተለያዩ ጊዜያት ያሰራጫቸው ሚጃዎች በግልጽ ያመለክታሉ፡፡

ይህ አቋማቸውም እነሱን ኢ-ሕገመንግሥታዊና ኢ-ዴሞክራሲያዊ በሆነ ማንኛውም ዓይነት መንገድ ሥልጣን ላይ የሚያወጣቸው እስከሆነ ድረስ በጸረ ሰላም መንገድ ምን ያህል እርቀት ሊጓዙ እንደሚችሉ ያጋለጣቸው ድርጊት ነው፡፡ እነሱ በተንደላቀቀ የውጭ አገር ኑሮ ወስጥ ሆነው በርቀት መቆጣጠሪያ በሚከታተሉትና በሚሾርቡት ተንኮልና ሴራ ሕዝብን ወደ እልቂት በማምራት በሕዝቡ ኪሳራ ለማትረፍ የሚንቀሳቀሱ ኃይሎች ናቸው፡፡ ይህን ዓይነት እንቅስቃሴ ለማድረግ ተማምለው የተደራጁ ጸረ-ሰላምና ጸረ-ልማት ኃይሎች ይህን አይነት እጅግ ዘግናኝ የእልቂት ድግስ አዘጋጅተው ሕዝብንና ሃገርን ጭዳ ለማድረግ በመወሰን መንቀሳቀሳቸውም ኃላፊነት የሚይሰማቸው ግለሰቦችና ቡድኖች ስብስብ መሆናቸውን በግልጽ የሚያመለክት ነው፡፡

እነዚህን ሦስት ድርጅቶችን /ኦብነግ፤ኦነግና ግንቦት ሰባትን/ በጋራ የሚያስተሳስራቸው ማዕረታዊ እውነታ የሚጣጨውም ዓላማቸውን ለማሳካት የወሰዱት የጋራ የጥፋት አማራጭ ነው፡፡ አማራጭ መወሰድ ብቻም ሳይሆን፤ ዓላማቸውን ለማሳካት የፈጸሙትና የተጓዘበት አቅጣጫ በቀጣይም እንከተለዋለን የሚሉት ስትራቴጂ በአመጽ፤በኃይልና በሽብር የታገዘ ስለሚሆኑ በራሳቸው ሚዲያጋገጫ ማግኘቱ የነዚህ ኃይሎችን አደገኛነት በግልጽ የሚያመለክት ነው፡፡ በዚህ አካሄዳቸውም በተግባር ራሳቸውን ከሽብርተኝነት ካምፕ ወስጥ የከተቱ መሆናቸው እንጂ መንግሥት እነሱን በሽብርተኝነት መመዝገቡ አንዳችም የተለዬ ጥቅምና እወቅና የሚያሰጠው ወይም የሚያሸልመው ሆኖ እንዳልሆነ በግልጽ ይታወቃል፡፡ ቀደም ሲል በነዚህ ኃይሎች ቀጥተኛ ተሳትፎ አለያም ድጋፍና ትብብር ጥቃቶች እንደተሰነዘሩ በተጨባጭ እስከተረጋገጠና በቀጣይም በዚሁ መንገድ እንደሚቀፉበት አሁንም ድረስ የራሳቸውን ሚረጋገጫ እየሰጡ ባለበት ሁኔታ ለሽብርተኝነታቸው ሌላ ምስክር ሚፈላለግን ወይም የተለዬ ዋቢ መጥቀስን የሚያሻ አይሆንም፡፡

ሌላው ቀርቶ እነዚህን ኃይሎች በቀጥታ የሚያስተባብራቸውና እያስታጠቀ የሚልካቸው በተለያዩ ሚልኩም ሁለንተናዊ ድጋፍ እያደረገላቸው ያለው ጸረ ኢትዮጵያ አቋም ያለውና የምስራቅ አፍሪካን ሰላምና ደህንነት በማወክና በማዙራመስ ዋነኛ ተዋናይ የሆነው የሻእቢያ መንግሥት መሆኑ ማዘንጋት የለበትም፡፡ ማዕረታዊ የትስስራቸው ድር እዚህ ላይ ይማዛዛል፡፡ ምንም እንኳ ዓላማቸው የተለያዩ እንደሆነ ቢለፍፉም በጸረ ሰላምና ጸረ ኢትዮጵያ አቋማቸው ላይ ግን የጋራ ግብ ያላቸውና ይህ የተግባር አንድነታቸውም ወደ ሽብርተኝነት ጥግ የደረሰ ተመሳሳይ የጥፋት ተልእኮ ይዞ ወደ መንቀሳቀስ ያደረሳቸው መሆኑ ዛሬ ከማንም የተሰወረ አይደለም፡፡

የኤርትራ መንግሥት ደግሞ ቢያንስ ቢያንስ አሁን ባለው እውነተኛ ባህሪይወና እያራመደው ባለው ጸረ ሰላም ፖሊሲው ለኢትዮጵያ ሕዝቦች በጎ ያስባል፣ለሰላምና ለሚልካም ጉርብትና በትብብር ይሰራል ተብሎ በምንም ሚልኩ ቢሆን አይታሰብም፡፡ በአንዳች ልዩ ተአምር በራሱ ላይ ማነረታዊና ሥር ነቀል የሆነ ወስጣዊ የለውጥ ተሃድሶ ካልመጣ፤አለያም በዋለና ባደረ ብሶት ከወስጥ በሚመጣ የለውጥ ነፋስ፤በሕዝቦችና በሰላም ኃይሎች የጋራ ትግል በኃይል ተገፍትሮ እስከወዲያኛው ካልወደቀ በስተቀር አሁን በተጨባጭ ያለው ተፈጥሮአዊ ባህሪው ይህን እንዲያደርግ አይፈቅድለትም፡፡ ሶማሊያ ወስጥ ለሚታየው አለመረጋጋት፤ለሕዝቦቿ እልቂትና ስደት፤ ብሎም ሃገራዊ ወድመት ዋነኛ ምክንያት ለሆነው የሽብርተኞች እንቅስቃሴ ቀጥተኛ ድጋፍ በማስጠትና በአጠቃላይም የአካባቢው ጎረቤት ሃገሮችን ሰላም በሚደፍረስ ባለው የጎላ አፍራሽ ሚና ምክንያት በዓለም አቀፉ ማህበረሰብ የተወገዘና በተመድም ማእቀብ የተጣለበት መሆኑ ይታወቃል፡፡

በመሆኑም በቅርቡ በሃገራችን በሽብርተኝነት የተፈረጁት ኦነግ፤ኦብነግና ግንቦት ሰባት ከሻእቢያ መንግሥት ጋር ያላቸው ትብብር፣ቁርኝትና መደጋገፍ በወል ሊጠኑ የሚገባው ነው፡፡ የለዬለት የኢትዮጵያ ሕዝቦች ጠላት በሆነ አፍራሽ ኃይል የቅርብ ክትትል፤ድጋፍና ትብብር የሚንቀሳቀሱ ጸረ ሕዝብና ጸረ ልማት ኃይሎች ለኢትዮጵያ ሕዝቦች አሳቢና ተቆርቋሪ ሊሆኑ ይችላሉ ተብሎ በፍጹም የሚታሰብ አይሆንም፡፡ በሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ መንገድ እንዲሁም ሕገመንግሥታዊ ሥርዓቱ በሚፈቅደው አግባብ በሃገሪቱ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ በነጻነት ከመሳተፍ ይልቅ፤ በአመጽ፤በኃይልና በሽብር ተግባር ማስሚራታቸው ከራሳቸው የትርምስ አጀንዳም ባለፈ የሻእቢያን ስወር ተልእኮ ለማስካት በግልጽ እየተነቀሳቀሱ ለመሆኑ አይነተኛ ሚረጋገጫነው፡፡

ሻእቢያ አልሸባብን ጨምሮ እነዚህን ቡድኖች የሚደግፈወና የሚያበረታታው የራሱን የ"ጭድ ሰል አልወድም" የትርምስና የብጥብጥ አጀንዳ በኢትዮጵያና ከዚያም ባለፈ በምስራቅ አፍሪካ ቀንድ ተፈጻሚ ለማድረግ እንጂ፤ በምንም ተአምር ለኢትዮጵያ ሕዝቦችና ለአካባቢው ሃገራት ቅን አሳቢ ሆኖ እንዳልሆነ መላ የኢትዮጵያ ህዝቦች፤ሰላም ወዳድ የዓለም ህብረተሰብ፤ አህጉራዊና ክፍለ አህጉራዊ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች በሚገባ ከተረዱት ቆይተዋል፡፡ ይህም ነው ዓለም አቀፍ ወግዘትና ማግለል ያስከተለበት፡፡

የኤርትራ መንግሥት የሃገር ወስጥ የሽብር ኃይሎችን ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ ደረጃም በሽብርተኝነት የተፈረጀወንና በሶማሊያ እየተፈጸመ ላለው ሽብር ዋነኛ ተጠያቂ የሆነወን አልሸባብና ሌሎች ጸረ ሰላም ቡድኖችን በሁለንተናዊ ሚልኩ በመደገፍና በማስታጠቅ ለሽብር ተግባር እንደሚያሰማራ ይታወቃል፡፡ አልሸባብና ሌሎች በሶማሊያ ወስጥ የሚንቀሳቀሱ ማነል የጥፋት

ሃይሎችም በአልቃይዳ በቀጥታ የሚደገፉና ጥብቅ ቁርኝትም ያላቸው ድርጅቶች ናቸው፡፡ ይህም ሻእቢያ በተመሳሳይ ሜሌኩ አልሸባብን እየደገፈ ያለ በመሆኑ በቀጥታና በተዘዋዋሪ ዓለም አቀፍ የሽብርተኛ ቡድኖችን በአጋርነት እንደሚደግፍና እንደሚያበረታታ የሚያመለክት ግልጽ ማሳያ ነው፡፡ እዚህ ላይ ነው እንግዲህ የእኛዎቹ የሃገር ወስጥ ጉዶች አነግ፤አብነግና ግንቦት ሰባት በሻእቢያ ፊታወራሪነትና ደጋሽነት በአንድ መድረክ ላይ ተገናኝተው ከአንድ ሜዕድና ጽዋ የሚቋደሱት፡፡ የተለያዩ ስም ይያዙ እንጂ የትስስራቸው ምንጭ መሳሻም ይኸው ገሃድ የወጣ ቋጠሮ ነው፡፡ ታዲያ ለነዚህ ቡድኖች የሽብርተኝነት ፍረጃ ከዚህ የበለጠ ምን ዋቢ ያስፈልገዋልና ነው አንዳንድ ኃይሎች የነዚህን ድርጅቶች እወነተኛ ማንነት ለሚድበሰበስ እየፋተሩ ያሉት ብሎ ማጠየቅ ተገቢ ይሆናል፡፡ አሶሜሪ ላይ በመሟሻግ ከጸረ ኢትዮጵያ ኃይሎች ጋር ሚኬራቸው በራሱ ብቻ ለዚህ ፍረጃ ያበቃቸው ሳይሆን፤ ቀደም ሲል በተግባር የፈጸሙት፤እየፈጸሙት ያለወና በቀጣይም እንሜራብታለን የሚሉት የጥፋት ስትራቴጂ ዋነኛው ነው፡፡ ይህን መካድ ተራራ ከሚያህለው የፊት ለፊት ግዙፍ እወነታና ከንጹህ ሕሊና ጋር መላተም ነው የሚሆነው፡፡

በአሜሪካ ላይ ያነጣጠረው የመጀመሪያው የአልቃይዳ የሽብር ጥቃት የተሰነዘረው እኤአ ዲሴምበር 29/1992 ሶማሊያ ወስጥ ሰብአዊ እርዳታ ለማስጠት ለተሰማሩ ዓለም አቀፍ ግብረ ሰናይ ድርጅቶች ጥበቃ በሚያደርጉ ወታደሮቿ ላይ ነበር፡፡ በጥቃቱም ሁለት የአወስትራሊያ ቱሪስቶች ለእለፈተ ሕይዎት ተዳርገዋል፡፡ በተመሳሳይ ቀንንና ስአት ላይም በየመን ኤደን አወሮፕላን ማረፊያ በነበሩ የአሜሪካ የጦር አወሮፕላኖች ላይ የሮኬት ጥቃት ለሚድረስ ተዘጋጅተው የነበሩ የአልቃይዳ ሽብርተኞች ጉዳት ከሚድረሳቸው በፊት በክትትል ሊያዙ ችለዋል፡፡ በመቀጠልም እኤአ ፌብሩዋሪ 26/1993 በኒዩርክ የዓለም ንግድ ሜዕከል ይገኝበት በነበረው መንትያ ሕንፃዎች ላይ የቦንብ ፍንዳታ ተፈጽሞ ስድስት ሰዎች ተገድለው 1 ሽህ 500 የሚሆኑ ቆስለዋል፡፡ ከስምንት ዓመታት በኋላ እኤአ ሴፕቴምበር 11/2001 በነዚሁ ሕንፃዎች ላይ በተፈመ ዘግናኝ የአይሮፕላን ላይ የአጥፍቶ መጥፋት ጥቃት (9/11) ሳቢያ 3 ሽህ 44 የሚሆኑ ሰዎች ሕይዎታቸወን አጥተዋል፡፡ በአንድ ጊዜ ጥቃት ይህን ያህል ሰዎች ሲገደሉ ከዚያ በፊትም ሆነ በኋላ የተፈጸሙ የሽብር ጥቃቶች ካደረሱት አጠቃላይ ጉዳት ከአስር እጥፍ በላይ የበለጠ እንደነበር መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ የአሜሪካ መንግሥት ጠበቅ ያለ የፀረ-ሽብርተኝነት ፖሊሲ ቀርጾ መንቀሳቀስ የጀመረወም ከዚህ ጊዜ በኋላ ነበር፡፡ በርካታ ሃገራትም ይህንኑ ተከትለው ሽብርተኝነትን በተቻለ ማጠን ለመከላከል የጸረ-ሽብርተኝነት ሕግ ከማውጣትና ከማጠናከር በተጨማሪ ሌሎች እርምጃዎችን በተናጠልና በይበልጥም በጋራ ትብብር መወሰድ ጀመሩ፡፡

የአሜሪካንን ሁኔታ እዚህ ላይ መጥቀስ የፈለኩት አንድ ነጥብ ይዤ ነው፡፡ ይኸወም በአሜሪካ ላይ ይህን ያህል ጉዳት ያደረሰው አልቃይዳ ነው፡፡ አነግ፤አብነግና ግንቦት ሰባት ከሰላማዊና

ዴሞክራሲያዊ ትግል ይልቅ የሃይልና የአመጽ ማንገድን በማምረጥ ከዚሁ ጋር ተመሳሳይ በሆነ ጎዳና እንደሚጓዙ በተግባር አረጋግጠዋል፡፡ የቅርብ ትስስራቸውና ቁርኝታቸው ደግሞ ጸረ ኢትዮጵያ ዓላማ አንግቦ ከሚንቀሳቀሰው ከሻእቢያ ጋር ነው፡፡ ሻእቢያ ማጡ ሰፊ ድጋፍና ትብብር እየሰጠው ያለው ሌላው የሽብር ቡድን ደግሞ አልሸባብ ነው፡፡ አነግና በይበልጥም ኦብነግ ለአልሸባብ ያላቸውን ቅርበትና የትግል አጋርነት በተለያዩ አጋጣሚ አረጋግጠዋል፡፡ አሸባሪው አልሸባብ ጸረ-ኢትዮጵያ አቋም ያለው ሲሆን፤ ከአልቃይዳም ቀጥተኛ ድጋፍ ያገኛል፡፡ ይህ የግንኙነት ሚብና ድልድይ የነዚህን ድርጅቶች የተባበረ ጸረ ኢትዮጵያ አቋም በግልጽ ያሚከታል፡፡

ከላይ በአሜካ ላይ የደረሰው የሽብር ጥቃት ማጡንና አድማሱን እያሰፋ መጥቶ በሜጨሻ ላይ እኤአ በ2001 እጅግ ዘግናኙንና (9/11) በሚል የሚታወሰውን አደጋ አስከትሏል፡፡ በሃገራችን በሽብርተኝነት የተፈረጁ ቡድኖችን /በተለይም የሃገር ወስጦችን/ ሽብርተኛ ናችሁ ለማለት የግድ የኒዮርኩን ዓይነት ወይም የዚያ ተመጣጣኝ የሆነ ጉዳት በሃገራችን እስካላደረሱ ድረስ፤ ይህም ባይሆን እንኳ "በተራቀቀ የሽብር ጥቃት የተካኑ" ሆነው አደገወና ጎልማሰው ምናልባትም የሃገር ወስጦቹ ዓለም አቀፍ እውቅና እስኪጎናጸፉና ይህን እስክናይ ለምን ሰማቸው ይነሳል? የሚል አይነት የሚናገሪያ አቋማቸውን ይዘው ከሰሞኑ ብቅ ያሉ ሰዎችን ሚታችን በእጅጉ የሚያሳዝን ነው፡፡ ይህ አመለካከት አሳፋሪና አሳዛኝ ከመሆኑም በላይ በሕዝብና በሃገር ደህንነት፤ሰላምና ጥቅም ላይ የተቃጣ የፕሮፓጋንዳ ጦርነት ከዚህም አለፍ ሲል በሃገርና በሕዝብ ላይ መቀለድና ማዛባበት ይሆናል፡፡

ቀደምወኑ ከዚህ በፊት ከነዚህ ድርጅቶች መካከል በአንዳንዶቹ ተቀነባብረው የተፈጸሙ የሽብር ጥቃቶችን በሚገባ እያወቁ፤ ሻእቢያ አልሸባብን ጨምሮ ለነዚህ ቡድኖች ተመሳሳይ ድጋፍና ትብብር እየሰጣቸውና አስመራ ወስጥ ጽ/ቤታቸውን ከፍተው በይፋ እንደሚንቀሳቀሱ ሚድረጉ እየታወቀ፤ዓላማቸውን በሃይልና በአመጽ ለማስፈጸም የሚጓዙበትን አግባብ በግልጽ እየተናገሩና ይህንኑ እየተገበሩ ባለበት ሁኔታና ከጸረ ኢትዮጵያ ኃይሎች የሚነጥፍ ድጋፍና ትብብር እየተደረገላቸው መሆኑንና ከዚህም አልፈው ለሻእቢያ የተላላኪነት ሚና እየተጫወቱ ያሉ መሆናቸውን በግልጽ እያወቁ ይህን ኃላፊነት የጎደለው ሃሳብ ማንጸባረቃቸው በእጅጉ አሳዛኝ ነው፡፡ ይህ የቡድኖቹ ተግባርና እንቅስቃሴም ራሳቸውን በሽብርተኝነት ለማስፈረጅ በሚያበቃ ሚለኩ መመዘኛዎችን የሚያሟሉ ለመሆኑ ግልጽና ተጨባጭ ማመላከቻዎች ናቸው፡፡

ቀደም ሲል በሃገራችን የተቃጡ የሽብር ጥቃቶች እኮ የወጭ ሃገር ዜጎችን ጨምሮ በርካታ ኢትዮጵያወያንን የሕይዎትና የአካል ጉዳት ሰለባ እንዳደረጉ እንደቷት ቢዘነጋ ነው ዛሬ ጉዳቱን ለፈጸሙ ቡድኖች ተቆርቋሪ ሆነው የቀረቡት? ይህ አመለካከታቸው ቢያንስ ቢያንስ በጉዳቱ ሰለባ

በሆኑ ንጹሃን ዜጎች ቤተሰቦችና በአጠቃላይም እንደ ዜጋ በሌላው የህብረተሰብ ክፍል የሚያሳድረው ተጽእኖ ምን ያህል ከባድና አሳዛኝ እንደሆነ ሊሰማቸው አለመቻሉን ሳስብ በበኩሌ ሰብአዊ ፍጡርነታቸውን እንድጠራጠር ያደርገኛል፡፡ ጉዳቱ በራሳቸው አለያም በቅርብ ዘመዶቻቸው ላይ ደርሶ ቢሆን ኖሮ አሁን የሚያቀነቅኑትን ጉንጭ አልፋ ማደናገሪያ እንደሚያነሱ በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል፡፡

ስለሆነም እነዚህን ድርጅቶች በሽብርተኝነት ለሚፈረጅ በራሳቸው ላይ ጉዳት ደርሶና ሰለባዎች ከሆኑ በኋላ/ለዚያውም በሕይወት የመትረፍ እድሉን ቢያገኙ ማለት ነው፤/ "አዎ ልክ ነው ሽብርተኞች ናቸው፤" እስኪሉን ማጠበቅ ያለብን አይመስለኝም፡፡ ይህ ቢሆን ኖሮ ደግሞ "አድኑን፤ ድረሱልን" አይነት ጩኸት ከያሉበት ተጠራርተው በማስተጋባት መንግሥት ሽብርተኞችን ለመቆጣጠርና እርምጃ ለመውሰድ ባለመቻሉ ዜጎች የሽብር ጥቃት ሰለባዎች እየሆኑ ነው፤ የሚል የአዞ እንባ አፍሳሽነት ድምጻቸውን ሊያሰሙ ይችሉ እንደነበር በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል፡፡ ከዳር ሆነው የእልቂት እሳቱን ማራገብና መቆስቆስ እንጂ እሳቱ ጫፋቸውን እንዲነካቸው በፍጹም አይፈልጉም፡፡

አንዳንዶችም ስለ ሽብርተኝነት ትርጉምና ስጋት ብለው የተለያዩ ሃገራትን የጸረ-ሽብርተኝነት ሕግና የአሰራር ልምድ በማንሳት "ሊተነትኑ"ና ይህንኑም ከሃገራችን ሁኔታ ጋር አያይዘው ሊያቀርቡ መሞከራቸው አልቀረም፡፡ የሚያሳዝነው ግን አንዳቸውም ቢሆኑ በሃገራችን ስለተፈጸሙ ጥቃቶችና በዚህም ስለደረሰው ጉዳት፤ከዚህም ጋር አያይዘው ድርጊቱን ስለፈጸሙት እነዚህ ኃይሎች ማንነት በግልጽ ለመናገር ድፍረቱን ማጣታቸው ነው፡፡ ታዲያማ ምነው እዚህ ላይ ስትደርሱ ሃቁን ለመናገር ወኔው ከዳችሁ? መልሱን ለራሳችሁ! እዚህ ላይ ነው እንግዲህ የጸረ ሰላም ኃይል ደጋፊነታችህን "ሂሳብ ማወራረድ" እንዳለባችሁ ግድ የሚሆንባችሁ፡፡

አንድ ድርጅት የፈለገውን ዓይነት ስምና ዓላማ ይያዝ፤ ምሎና ተገዝቶ ሕዝባዊ ነኝ ይበል፤ ዋናው መታየት ያለበት ግን ዓላማውን ለማስፈጸም የያዘው ስትራቴጂና አቅጣጫ እንዲሁም ተግባራዊ እንቅስቃሴው ነው፡፡ ተግባር ከሚያረጋግጠው ውጭ የራስን ርክሽ ዓላማ ተፈጻሚ ለማድረግ ሲባል ብቻ በሕዝብ ስም የ.....ነፃ አውጪ፤የ......ግንባር፤የ.....እንቅስቃሴ፤የ.....ድርጅት ወዘተ የሚሉ አስመሳይ ስያሜዎችን /ታፔላ/ በመለጠፍ ብቻ ሕዝባዊነትን መላበስ ፈጽሞ አይቻልም፡፡ በተጨባጭ ከነዚህ ድርጅቶች ያየነውና ያረጋገጥነው እውነታም ስሙን ከመያዛቸው በስተቀር ከዚህ ውጭ ባለመሆኑ ምንም አይነት ቀለም /ከለር/ ቢቀቡ እውነተኛ ማንነታቸውን ከሕዝብ ሊደብቁት አይችሉም፡፡ በተለያዩ ጊዜያት የሽብር ጥቃት ማድረሳቸውና አልፎ አልፎም ገና በእንቅስቃሴ ላይ እንዳሉ በህብረተሰቡ ጥቆማ በጸጥታ ኃይሎች የቅርብ ክትትል ተደርሶባቸው የተያዙ አባላቶቻቸው ድርጊቱን የፈጸሙት በራሳቸው የግል ተነሳሽነት

ሳይሆን፤ የድርጅቶቻቸውን ተልእኮ ይዘው እንደነበር በራሳቸው የምስክርነት ቃልና በሚዲያ የተረጋገጠ እንደነበር ሁላችንም የምናስታውሰው ነው።

ከዚህም ባለፈ ከጸረ-ኢትዮጵያ ኃይሎች ጋር በማናኘት በሃገርና በሕዝብ ላይ ሚኬራቸው ብሎም ከሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ ትግል ይልቅ በነውጥ፤በሽብርና በኃይል ሕገ-መንግስታዊ ሥርዓቱን ለማፍረስ፤የሕዝብንና የሃገርን ሰላምና ጸጥታ ለማወክ ግልጽ ዓላማ ይዘው መንቀሳቀሳቸው የሽብር አራማጆች ለመሆናቸው ግልጽ ማሳያ ነው። በሃገራዊ ዋና ዋና ጉዳዮችና አጀንዳዎች ላይ የጋራ መግባባትን በማያዝና በኃላፊነት መንፈስ ሃገራዊ የዓላማ አንድነትን በማጎልበት፤ በሌሎች ሚዛን በሚደፉና ፋይዳ ባላቸው ፖለቲካዊ የሃሳብና የአመለካከት ልዩነቶችና እምነቶች ላይ ደግሞ ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱና ሌሎች የሃገሪቱ ሕጎች በሚፈቅዱት መሰረት ሃሳብንና አመለካከትን በሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ መንገድ ማንሸራሸር ሲቻል፤ ከዚህ በተጻራሪው መንቀሳቀስ ግን የሕዝቡን መብትና ጥቅም መጻረር ነው የሚሆነው።

በአንዳንድ ወሳኝ ሃገራዊና ሕዝባዊ ጉዳዮች ላይ መሰረታዊ ልዩነቶች ቢኖሩ እንኳ፤እንደሁኔታው በህዝበ ውሳኔ እልባት እንዲያገኙ እስከሚጠየቅ ጥግ ወይም ጫፍ የደረሰ የሕዝቦች መብት በተከበረበት ሃገርና መንግሥታዊ ሥርዓት ውስጥ በምንም መልኩ ቢሆን በሽብርና በነውጥ የራስን ዓላማና ፍላጎት በሕዝብ ላይ በኃይል መጫን የሚፈቀድ አይሆንም። ሕዝባዊ መሰረትና ድጋፍም ፈጽሞ አያስገኝም። እዚህ ላይ በጣም ጥቂት ተቃዋሚ ፓርቲዎችን ጨምሮ አንዳንድ ጸረ ሰላም ኃይሎችና ግለሰቦች እየሰጡት ያለው አስተያየት ሽብርተኝነትን ለሚያራምዱና ለሚያበረታቱ አካላት ለምን ሕጋዊ እውቅና አይሰጣቸውም የሚል ዓይነት ድምዳሜ እንደምታ ያለው ነው። ይህ በእውነቱ ኃላፊነት የጎደለው አሳፋሪ አመለካከትና አቋም ነው። የነዚህ ቡድኖች ዓላማ በአጭሩ በሽብርና በነውጥ ጋጋታ ሕገመንግሥታዊ ሥርዓቱን በኃይል በማፍረስ በሚፈጠረው ማንኛውም ቀዳዳ ሥልጣን ላይ መውጣትና ሕዝቡን በተጽእኖአቸው ሥር ማዋል ነው። ሕዝባዊና ሃገራዊ ዓላማ አላቸው ብሎ ማሰብም ተፈጥሮአዊ ያልሆነ ከእባብ እንቁላል የእርግብ ጫጩት የማጠበቅ ያህል ነው። በሕጋዊ አለያም ሕጋዊ ባልሆነ የፖለቲካ ድርጅት ሽፋን ጸረ ሰላምና ጸረ ሕዝብ ተግባር ሚራመድና ለዚህ ዓይነቱ ተግባር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተባባሪ ሆኖ ማኘትም ከተጠያቂነት አያድንም። ይህ ተፈጽሞ ሲገኝ ደግሞ እንደሁኔታው በግልና በድርጅትም አለያም የተናጠልና የጋራ ሕጋዊ ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል። ይህ ደግሞ ተቀባይነት ያለው ዓለም አቀፋዊ መርህና ሕጋዊ አሰራር ነው።

በመሆኑም የነዚህ ድርጅቶች መሰረታዊ ችግር በዋናነት የሚያጨው ከስማቸው ወይም የምንታገለው ለ"ሕዝብ" ነው ከሚለው ማስመሰያቸው ሳሆን፤በተግባር ከሚከተሉትና ከሚያራምዱት የዓላማ ስኬት ስትራቴጂ ነው። ይህም የነዚህ ቡድኖች እውነተኛ ማንነት፤የእርስ በርስ ትስስርና ብልሽት እንደ

እንቁላሉ ከወስጥና እንደ አሳወም ከጫቅላት በመሆኑ በሕዝብና በሃገር ላይ ከሚያደርሱት ጉዳት ወጪ አንዳችም ፋይዳ ያለው አስተዋጽኦ ይኖራቸዋል ተብሎ አይታሰብም፡፡

ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ ተሳትፎ ሚድረግ እንደሚቻል አምነውና በቀደመው ተግባራቸው ተጸጸጽተውና ድርጅቶቻቸውን አወግዘው ወደ ሰላማዊ ኑሮአቸው የተመለሱ በርካታ የኦነግና የኦብነግ አባላት እንደመኖራቸው፤ በጥቂቶችና ከነርሱም ወስጥ በተለያዩ አንጃዎች ተከፋፍለው በሽብርተኝነት በተሰማሩ ጥቂት ጋሻ ጃግሬዎች የሚሞሩትን እነዚህን ጸረ ሰላም ኃይሎች መላው የኢትዮጵያ ሰላም ወዳድ ሕዝብና መንግሥት በቀጣይም በጽናት እንደሚዋጋቸው ሊታወቅ ይገባል፡፡

ማንም ቢሆን ከሕግ በላይ ሊሆን አይችልምና መንግሥት እስከሚጨረሻው እርቀት ተጉዞ የሃገርንና የሕዝቡን ሰላምና ደህንነት የሚረጋገጥ ኃላፊነቱን በአግባቡ ሊወጣ ይገባል፡፡ ከዚህ በተጻራሪው መንግሥት የስጋት ምንጮችን በመከታተል ወቅታዊ እርምጃ ሳይወስድ ቢቀር ግን፤ማዛዙ ለሁሉም የሚተርፍና በሕብረተሰቡ የእለት ተእለት ማህበራዊ ኑሮ፤ሰላምና ደህንነት ላይ በድምሩም የሃገር ህልወናን አጠየያቂ የሚያደርግ አደገኛ ክስተት ሊያስከትል እንደሚቻል ጥልቅ ግንዛቤ ሊያዝበት ይገባል፡፡ ሕዝባዊነት ምንጊዜም አሸናፊ ነወና የነዚህ ጸረ ሰላምና ጸረ እድገት ኃይሎች ዓላማ በምንም ሜልኩ ቢሆን የሚከካ አይሆንም፡፡ የጸረ ሽብርተኝነት ትግላችንም ዓለም አቀፋዊ ድጋፍ ያለው በመሆኑ ዓላማችን ምን ጊዜም አሸናፊ ነው፡፡

ታዲያማ እነዚህ ቡድኖች የያዙት ስም ብቻወን ማንነትን አይገልጽም፡፡ እውነተኛው ማንነታቸው ከስማቸው ጀርባ ያለው ጸረ–ሰላም ተግባራቸው ያረጋገጠው ነወና ሕዝባዊ፤ዴሞክራሲያዊና ሰላማዊ ነን ብሎ ለመናገር ምንም አይነት የመከራከሪያ ነጥብ ሊያነሱ የሚያስችላቸው አንዳች ሕጋዊ መሰረትና መብትም ሆነ ሞራላዊ ብቃት የላቸወም፡፡ ሽብርተኝነትን እንደ ዓላማ ማስፈጸሚያ ዋነኛ ስልትና አማራጭ በማያዝ የሚንቀሳቀሱና አዋላጆቻቸውም ይዋል ይደር እንጂ በሕዝባዊ ዓላማ የሚጨረሻወን ሚራር ጽዋቸወን መጋታቸው አይቀርም፡፡ ስለሆነም የነዚህን ጸረ–ሰላምና ጸረ–ልማት ኃይሎች እውነተኛ ማንነት በሚጋለጥ እስከሚጨረሻው ለማታገልና ብሎም ሰላምን በሚረጋገጥ ልማትን ለማፋጠን ሁሉም የሰላም ኃይሎች በጽናት ተባብረው መቆም ይኖርባቸዋል፡፡ ነገሩስ አበው እንዳሉት "ሳይቃጠል በቅጠል" አይደል፡፡